# የደቂቀ እስጢፋኖስ ዐውደ ንባባዊ ትንታኔ

ፍሬህይወት ባዩ[1]


**አኅጽሀሮተ ጽሁፍ**

የዚህ ጥናት ትኩረት ደቂቀ እስጢፋኖስ("በህግ አምላክ") በሚል ርዕስ በጌታቸው ሀይሌ ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ለሁለተኛ ጊዜ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ፕሬስ የታተመ መጽሀፍ ነው። የአባ እስጢፋኖስና የተከታዮቻቸው ገድል በጥቅሉ ደቂቀ እስጢፋኖስ ተብሎ አራት ገድሎችን በአንድ ጥራዝ አካቶ ለህትመት በቅቷል። የጽሁፉ ዋና አላማ ደቂቀ እስጢፋኖስን በዐውደ ንባባዊ ስልት መተንተን ይሆናል። በደቂቀ እስጢፋኖስ ገድል ውስጥ የተካተቱት ገድሎች የ15ም/ክ/ዘ ኢትዮጵያዊያን በተለይም የሃይማኖት መጻህፍትን በማንበብ በመጻፍ እና በመመራመር የላቀ አስተሳሰብ እንደነበራቸው የሚጠቁሙ ናቸው። አባ እስጢፋኖስ እና ተከታዮቻቸው ከአጼ ይስሀቅ ጀምሮ እስከ አጼ ናኦድ ድረስ በነበረው ንትርክ ከደረሰባቸው መከራ ተነስተው ገድላቸውን የጻፉት ተከታዮቻቸው ናቸው። በገድላቸው ውስጥ የምናየው በዘመኑ የነበረውን የማሰብ ነጻነት ጠቋሚ አሻራዎች ነው። ይህም ጥናት በአውደ ንባባዊ ስልት ገድሉ ውስጥ የተነሱ ኮዶችን በማፍታታት "ሀሳብን በሀሳብ እና ሀሳብን በስልጣን መርታት" የሚል አብይ ጭብጥ ተለይቶ ወጥቶለታል። የአባ እስጢፋኖስና የተከታዮቻቸው ገድሎች እንደ ሌሎች ገድሎች ዐውደ ንባቦቹ የሃይማኖት ናቸው። በአውደ ንባቦች ውስጥ ያሉት ድርጊቶች ሁነቶች እና ሁኔታዎች ሃይማኖታዊ ናቸው። ሆኖም በእምነት አይን አይተን በእምነት ጆሮ ሰምተን በእምነት ልቡና አምነን ይሁን ብለን የምናስተናግደው ብቻ አይደሉም። ስለዚህ ደቂቀ እስጢፋኖስ ከገድልነቱ እና ከስነጽሁፍ ቅርስነቱ ባሻገር በተለያየ የሙያ መስክ ቢጠና፣ ማስረጃዎችን ለይቶ በማውጣት ለሌሎች የጥናት መስኮች ግብአት በመሆን ያገለግላል።


[1] አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ፣ የፎክሎር ተመራማሪ

## ፩.መግቢያ

ደቂቀ እስጢፋኖስን(አራቱን ገድላት) እጅግ ባማረ ቋንቋ እና አቀራረብ ተርጉመው (ከግእዝ ወደ አማርኛ) ያዘጋጁልንን እንዲሁም ሰፋ ባለ መግቢያ እና በግርጌ ማስታወሻ የሰላ ትንተና ጨምረው ግእዝ ለማንችለው አንባቢ እንድናነበው እድል የሰጡንን ፕሮፌሰር ጌታቸው ሀይሌን እድሜ ከጤና ጋር ይስጥልኝ እያልኩ ላመሰግናቸው እወዳለሁ።

የአባ አበክረዙን ገድል በተጻፈበት ዘመን "ገድል" በአፍ ሙሉ ለግእዝ ስነ ጽሁፍ አዲስ ነው ባይባልም በሰፊው ይተረጎም፣ በሀገር በቀል ድርሰትነትም ይደረስ ነበር። ሌሎቹ ጸዋትው"ተአምር"፣ "ድርሳን"፣ "ውዳሴ"፣ "ቅዳሴ"፣ "መልክዕ"፣ "ስንክሳር" በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ "ሃይማኖታዊ" ከምንላቸው ውጭ "ዜና መዋዕል"፣ "ታሪከ ነገስት"፣ የፍልስፍና መጻህፍት "ታሪክ' (ለምሳሌ አባ ባሕርይ ስለ ኦሮሞ ህዝብና ስለሥርዓቱ የጻፈው) "ሐተታ" (ለምሳሌ የዘርያእቆብ አክሱማዊ እና የወልደ ሕይወት እንፍራዛዊ ሐተታዎች)። "ሕግ" ለምሳሌ ፍትሐ ነገስት፣ ዓምደ ጽዮን አጻፈው የሚባለው ሥርዓተ ህግ ወዘተ ናቸው። እንደ ቀደመው የአክሱም ዘመን በዚህኛውም ዘመን ሃይማኖቱ ፖለቲካው እና ስነ ጽሁፉ የተዛነቁ ወይም የተቆራኙ በመሆናቸው ጽሁፎቹ ሲጠኑ ከሶስቱም አንጻር ይሆን ዘንድ የዘመኑ አውድ የግድ የሚል ይሆናል። ማለትም፣ እዚህ ላይ ሃይማኖቱ፣ እዚያ ላይ ፖለቲካው፣ እዚህ ላይ ኪነቱ ብለን ለመለየትና ነጣጥለን ለማየት የጊዜው ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ርዕዮተ ዓለማዊ ሁኔታ አስቸጋሪ ያደርግብናል። <u>ስለዚህም</u>፣ ቅኚታችን (approach)ታሪካዊም፣ ፖለቲካዊም፣ ሃይማኖታዊ/ ፍልስፍናዊም (theological/philosophical)፣ ባህላዊም፣ ርእዮተ ዓለማዊም(ideological)፣ ምግባራዊም (ethical)፣ ሊሆን ይችላል። ኪነታዊ ከሁሉም ሊለቀም የሚችል ነው።

አብዛኛው የዓለም ህዝብ የጽሁፍ ጥበብን በቅርቡ የጀመረ ነው፡፡ ስለዚህም ቃላዊ ህዝብ ወይም ታሪኩን ባህሉን አጠቃላይ የኑሮ ዘይቤውን ሲያስተላልፍ የኖረው በቃል ነው ማለት ይቻላል፡፡ በቃል ሲተላለፍም የሚረሱ ጨርሶ የሚጠፉ መረጃዎች ይኖራሉ፡፡ መረጃዎች ዘመን ተሻግረው ለትውልድ እንዲተላለፉ በጽሁፍ መስፈራቸው ያለው ጠቀሜታ የሚያጠያይቅ አይሆንም፡፡ በሀገራችን በተለይም አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው በኖሩበት በ15 መ.ክ.ዘ የነበረውን የጽሁፍ ጥበብ ስንመለከት፣ የጽሁፍ ቋንቋ ምን ያህል አድጎ እንደነበረ የሚያሳይ ነው። ደቂቀ እስጢፋኖስ በኢትዮጵያዊ ጸሀፊያን በግዕዝ ቋንቋ ከተጻፉ ገድላት ለየት ያለጠባይ አላቸው። ለምሳሌ፣ በአጻጻፍ

ቴክኒክ፣ ድርጊቱ ተፈጽሞ ሳይረሳ በተሳታፊዎቹ(በባለቤቶቹ) እና በቅርብ ሰዎች መጻፉ፤ የገድሉ ተርጓሚ በመጽሀፉ መግቢያ እንዲሁም በግርጌ ማስታወሻ በሰጡት ማብራሪያ የሚጠቀሱ ናቸው።

አባ አበክረዙን ዛሬ ላለነው ትውልድ በመከራ ውስጥ ማለፋቸውን እንድናውቅ ይፈልጉ እንደነበር ገድላቸው ይነግረናል። “ከናንተ በኋላ ለሚመጡ ምስክር እንዲሆን አይተውም እንዲደሰቱበትና እንደዚያ እንዲያደርጉ ከእናንተ በፊት ስለነበሩት ወንድሞቻችሁ ገድልና ጻማ[2] ሁሉ አሁን ጻፉ[3]።” በማለት የጽሁፍ ጥበብ ምን ያህል የተለመደ እና የዳበረ እንደሆነ የመነኮሳቱን አርቆ አሳቢነት እናይበታለን። የገድሉ መጻፍ ዋና አላማ የአባ አበክረዙንን ተጋድሎ ለመዘከር ነው። ሆኖም ከገድላቸው ባሻገር እንደ አንባቢው የሙያ መስክ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ጠቃሚ መረጃ የሚሰጥ ነው፡፡ የደቂቀ እስጢፋኖስ ገድል አንባቢ የኢትዮጵን ታሪክ የዘመን አሻራ ይመለከትበታል።

የጥናቱ ዋና አላማ በአባ አበክረዙን ገድል ላይ አውደ ንባባዊ ትንታኔ ማቅረብ ነው። የመጽሀፉን አብይ ትኩረት ከአውደ ንባቡ ለማውጣት በገድሉ ውስጥ የተጠቀሱ የተለያዩ ኮዶችን[4] በመምረጥ መተንተን ያስፈልጋል።

ደቂቀ እስጢፋኖስ የመጽሀፉ ርእስ ሲሆን ገድለ አባ እስጢፋኖስ፣ ገድለ አበው ወአኀው፣ ገድለ አባ አበክረዙን እና ገድለ አባ ዕዝራ ከግእዝ ወደ አማርኛ የተተረጉሙትን አራት ገድሎች በአንድ ጥራዝ ይዟል። የዚህ ጥናት ትኩረት ገድለ አባ አበክረዙን (ገጽ 225-276) ላይ ብቻ ያተኩራል። ሌሎቹ ሶስት ገድሎች ለአባ አበክረዙን ገድል ማናበቢያ በመሆን ያገለግላሉ። ልብ ሊባል የሚገባው በደቂቀ እስጢፋኖስ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ሶስት ገድሎች ለተጋድሏቸው መነሻ የአባ እስጢፋኖስ ፈለግ ነው። ለዚህ ጽሁፍ ሁሉንም መመርመር ሰፊ ስለሚሆን ጥናቱ በአባ አበክረዙን ገድል ላይ ብቻ ተገድቧል።

---

[2] “ጻማ” ማለት “ድካም” ማለት ሲሆን መነኮሳት እግዚአብሄርን ለመለማመጥ ራሳቸውም ሆኑ ሌሎች የሚያመጡባቸው መማቀቅ ነው፤ ለጽድቅ ሲሉ ሰውነታቸው ድቅቅ እስኪልና እስኪደክም ድረስ ይጾማሉ፤ ለሃይማኖታቸው በእስር ቤት ይማቅቃሉ። የሰማይ ቤቱ ዋጋ በጻማው መጠን እንደሆነ ይታመንበታል። ጻማ “የድካም ፍሬ” ማለትም ይሆናል። “ጻማችንን ቀሙን” ማለት “ደክመን በላባችን ያገኘነውን ወሰዱብን” ማለት ነው (ደቂቀ እስጢፋኖስ51) ።

[3] ደቂቀ እስጢፋኖስ፡ 265

[4] “the code” ለምናሄደው ትርጓሜ፣ ለምንዘረጋው የሀቲት ጉባኤ ቁልፍ ሀሳብ(ዮናስ አድማሱ የክፍልውስጥ ዳረጎት(ማስታወሻ)2000)።

የጥናቱ ስልት ዐውደ ንባባዊ ትንተና(textual analysis) የተከተለ ነው። ተግባቦታዊ ሂደቱ የሚከናወንበት ጊዜ፣ ቦታ እና ተግባቦቱን ያመነጨው ዓቢይ ጉዳይ ዓውድ ይባላል (ብርሃኑ 1995፡6)[5]፡፡ ዐውደ ንባብን ለዚህ ጥናት እንዲመች አጥብበን ስንመለከተው፣ ዐውደ ንባብ (context)የሚጠናው ቴክስት የቀረበበትን ዐውድ ለማሳየት ነው። ነገር ግን አንድ ቴክስት ሲጠና ሌላ ቴክስት ስለሚያስፈልገው፣ የሚመጣው ቴክስት በዋናነት ለሚጠናው ቴክስት ማናበቢያ ስለሚሆን የአውደ ንባቡን ትርጉም (inter textual) ይጨምራል። በዚህ ስልት ትንታኔው የዐውደ ንባቡ አካል ይሆናል። ገድለ አባ አበክረዙን ዐውደ ንባብ በቀጥታ ቴክስትን የሚመለከት ነው። ከቴክስትም በጽሁፍ የቀረበ ገድልን ብቻ የሚመለከት ነው። ገድለ አባ አበክረዙን ዐውደ ንባቡ የሃይማኖት ነው። በአውደ ንባቡ ውስጥ ያሉት ድርጊቶች ሁነቶች እና ሁኔታዎች ሃይማኖታዊ ናቸው። በእምነት ዓይን አይተን በእምነት ጆሮ ሰምተን በእምነት ልቡና አምነን ይሁን ብለን የምናስተናግዳቸው ናቸው። ገድል ውስጥ ያሉ የተለያዩ ኮዶችን መልካቸውን ትተን ጠባያቸውን ከተመለከትን፤ ድርጊቶችን ሁነቶችንና ሁኔታዎችን ሳይሆን የድርጊቶቹን የሁኔታዎቹን ውስጣዊ ባህሪያት ከመረመርን የገድሉን መነሻ እና መድረሻ እንለያለን።

## 2.የጽንሰ ሀሳብ መነሻ

**ገድል**፡-ትግል፣ ፈተና፣ ውጊያ፣ ሰልፍ፣ ድልና አክሊል እስኪገኝ ድረስ የሚደክሙት ድካም፣ የሚሰሩት ስራ፣ የሚቀበሉት መከራ፣ መንፈሳዊ ዜና ወግ ታሪክ የቅዱሳን መከራ ፀጋ ተጋድሏቸውን የሚናገር ጽሁፍ ነው(ኪዳነ ወልድ 1948፡ 301)[6]።

ክሮው ፎርድ ደግሞ ገድልና ሚትን አቃይጦ ገድላዊ-ሚት ይለዋል። ቅዱሱ በእውን ኖሯል ብለን ካሰብን ገድላዊ ሚት ነው። ተራኪዎች ሚታዊ ጭብጦችን ይጨምራሉ[7]። በማለት በእውን ኖሯል ብለን ካሰብን የሚለው አፈ-ታሪክንም እንደሚጨምር የሚጠቁም ነው። የዚህ ጽሁፍ ጉዳይ የሆነው ቅዱስ አባ አበክረዙን ለተጋድሏቸው መሪ መምህር ከነበሩት ከአባ እስጢፋኖስና ከሌሎቹም ገራ በእውን በዚህ ዓለም ነበሩ። ለዚህም ማሳያ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከንጉስ ዘርያዕቆብ ጋራ በነበረው የሃይማኖት ክርክር የሚታወቅና አስተምህሮውም ዘመን የተሻገረ እንደሆነ ተርጓሚው ጭምር በመቅድማቸው ጠቁመውናል። ለምሳሌ፡-“ከረጅሙ ታሪካችን

[5] ብርሃኑ ገበየሁ (1999)፡፡ የአማርኛ ሥነግጥም፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

[6].ኪዳነወልድ ክፍሌ። መፅሐፈ፡ ሰዋሰው፡ ወግስ፡ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ 1948።

[7] Crawford, VM 1961 The legends of the saints: An introduction to Hagiography: translation from French.(6)

ውስጥ ለዛሬ እነዚህን ገድሎች የመረጥኩት ደቂቀ እስጢፋኖስ ከእኛ ዘመን በፊት ለእምነታቸው ምሳሌ የሌለው ከፍተኛ ትግል ያሳዩ ሆነው ስላገኘኋቸው ነው።" ሲሉ በእውን ስለመኖራቸው ለሚነሳው ጥያቄ ምላሽ ይሰጣሉ። ከኢትዮጵያ የታሪክ ምሁራን መካከል የደቂቀ እስጢፋኖስን ቀዳሚ ቃል የጻፉት[8] "ይህ ገድል በሚቀጥለው ንጉስ ዘመነ መንግስት (1468-1478 እአአ)ነገሩ ተፈጽሞ ገና ሳይረሳ ከአጭር ጊዜ በኋላ ስለተጻፈ ተአማኒነቱ ከፍተኛ መሆኑን እርግጠኛ መሆን ይቻላል(ደቂቀ እስጢፋኖስ 16)። በማለት ወይም በገድል ብያኔ በተለይ ከአፈታሪክ እና ከሚት ጥናት ጋር ተያይዞ የአባ እስጢፋኖስ በአንድ የታሪክ ዘመን በእውን ስለመኖራቸው ጥያቄ የማያስነሳ እና እንዲያውም ከሌሎቹ ገድሎች የበለጠ ተአማኒነት እንዳለው እና የገድሉን ታሪካዊ ማስረጃነት የማያጠያይቅ መሆኑን ይጠቁሙናል።

አንድ ተጋዳሊ ተጋዳሊ ለመሆን ይዞ የሚነሳው አላማና ለስኬቱ ሲል የሚያልፍባቸው አባጣ ጎባጣ መንገዶች አሉ። አላማው ፖለቲካ፣ ሃይማኖት ወይም ሰብአዊነት ሊሆን ይችላል። አባ አበክረዙንን ቅዱስ ያስባለው ገድል የተጻፈለት ለሚከተለው ሃይማኖት ከእርሱ የቀደሙ የሃይማኖቱ ተከታዮች በደነገጉትና በጽሁፍ ላሰፈሩት ቀኖና ታማኝ በመሆን ነው። ምድራዊው ተጋድሎ ከሞት በኋላ አለ ለሚለው ዓለም ለሙብቃት የሚደረግ ትግል ነው። ትግሉን ማሸነፍም ከሞት በኋላ ባለው ዓለም በተድላ ዘላለማዊ መሆን ነው።

## 3. ገድለ ደቂቀ እስጢፋኖስ አውደ ንባባዊ ትንታኔ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ቀኖና መሠረት ምድራዊ ተጋድሎን በአግባቡ ተወጥቷል የተባለ ግለሰብ "ቅዱስ" ተብሎ ገድሉ ይጻፋል። ሆኖም የአባ አበክረዙንን ገድል ለየት የሚያደርገው ስለ አባ አበክረዙን ቅድስና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ያላት አቋም እና በሃይማኖቱ ተከታዮች መካከል ያለው የተለያየ አቋም ነው። አንደኛው አቋም አባ አበክረዙን 'ቅዱስ አይደሉም'፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አታውቃቸውም እንዲያውም ተወግዘዋል የሚሉ ናቸው። የደቂቀ እስጢፋኖስ ተርጓሚም "ታሪካቸውን እዚህ የማቀርበው አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው (ደቂቀ እስጢፋኖስ)የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የማትቀበላቸው እንዲያውም የተወገዙ አድርጋ የምታያቸው በአስራ አምስተኛው ምእተ አመት ያበቡ ... ናቸው።" በማለት በመቅድማቸው ጠቁመዋል። ሁለተኛው አቋም ገድሉን የጻፉት እና ተከታዮቻቸው አባ እስጢፋኖስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ነበሩ። በዘመኑ የነበሩት በአባ እጢፋኖስ

[8] ፕሮፌሰር ሽፈራሁ በቀለ።

ገዳም የነበሩ መነኮሳት ጭምር ለግል ጥቅማቸው ሲሉ በሃይማኖት ሽፋን አባ እስጢፋኖስን እና ተከታዮቻቸውን እነ አባ አበክረዙንን ለሰማእትነት አበቋቸው እንጂ በአባ እስጢፋኖስና ፈለጋቸውን የተከተሉ መነኮሳት የሃይማኖት ህጸጽ የለብንም ብለው ያምናሉ። ስለዚህ አባ እስጢፋኖስንም ሆነ ተከታዮቻቸው የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች እንዲያውም በዘመኑ ከነበሩት የንጉሱ ተከታይ መነኮሳት የተሻሉ ለቅድስና የበቁ ናቸው የሚል አቋም የያዙ ናቸው።

ገድሉን የጻፉትን ወይስ ያወገዙትን እንቀበል? የሚለው የሚያወዛግብ ጥያቄ ነው። ለምሳሌ አባ እስጢፋኖስ የነበሩበት ገዳም ዛሬም በቤተ ክርስቲያኗ የሚተዳደርና ይህ ጽሁፍ የሚቀርብበት የደቂቀ እስጢፋኖስን ገድል ከግእዝ ወደ አማርኛ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኀይሌ ከተረጎሙ በኋላ የጉንዳጉንዶ ገዳም የአባ እስጢፋኖስን ገድል[9] አሳትሟል። "...ሊገመት የሚያዳግት ስደትና ስቃይ ቢደርስባቸውም፣ ገዳማቸው ዛሬም አለ። መነኮሳትም አሉበት። እስካሁን በልዩ ልዩ ምክንያት ተራቁተውባቸው ካልሆነ ... የተረጎምኩዋቸው ገድሎች ሁሉም የተገኙት ከነሱ ገዳም ነው። በአቋም ወይም በእምነት ረገድ ከሌሎቹ ገዳማት በምን እንደሚለዩ ግልጽ የሆነ ነገር የለም።" ሲሉ ገልጸዋል። ስለገድልነቱ "ገድለ" ብሎ የሚጀምረው የመጽሀፉ ርእስ አንዱ መረጃ ሲሆን ሁለተኛ ገድሉ የኢትዮጵያ ጸሀፊያን እንደ ደረሷቸው የተለመደ መግቢያ "በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" ይልና፣ "...የብፁዕና የቅዱስ፣ የሃይማኖት ዓምድ የክርስቲያን መብራት (የሰማእትነት) አክሊል የደፋ...የአባ እስጢፋኖስ ገድልና ሰማእትነት (እነሆ)(ገጽ56[10])" በማለት ይጀምራል።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አባ እስጢፋኖስን ከቅዱሳኗ መካከል ባታሰፍራቸውም ገድሉን የጻፉትና ተከታዮቻቸው ቅዱስነታቸውን አምነው ገድል ጽፈውላቸዋል። ስለዚህ በገድሉ ጸሀፊዎች እምነትና አቋም መሠረት ከላይ የተቀመጠውን የገድል ብያኔ[11] ተከትለን መጽሀፉን እንመረምራለን። አንድ ሃይማኖታዊ ተጋዳሊ አላማው የማይታየውና ተስፋ የሚያደርገው ዘላለማዊ ህይወት ነው። ከሞት በኋላ እደርስበታለሁ ብሎ ለሚያምነው ዘላለማዊ ህይወት ለመድረስ በአካልም በመንፈስም ከፍተኛ ተጋድሎ ያደርጋል። የአባ እስጢፋኖስ ተከታይ እና

[9] ከገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ(ዘአጠሞ መምህር ወማህበር ዘጉንዳጉንዶ ደብረ ገሪዛን ማሪያም ገዳም፣ 1996።

[10] ከዚህ በኋላ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ከአባ እስጢፋኖስ ገድል የምጠቅሰውን ማስረጃ በቅንፍ ገጹን ብቻ እጽፋለሁ።

[11] ቤተ ክርስቲያኗ ጋራ ያለው የአባ እሰጢፋኖስን ገድል መቀበል አለመቀበል የዚህ ጥናት ጉዳይ ስላልሆነ ከዚህ በላይ ማለቱ ከጥናቱ አላማ አኳያ ተገቢ አይደለም።

በአንድ ዘምን ብዙ መከራን የተቀበሉት አባ አበክረዙን ተጋድሎም ዘላለማዊ የሆነውን ህይወት ለመውረስ ነው።

የአባ አበክረዙን ገድል ጸሀፊ መግቢያ ግጥም ነው። "ከደብረ ገርዜን መንጋ እረኛ ነው" ሲልም ይነግረናል። አባ ናዕዴር ከምትባል ከአክሱም ቀበሌ፣ ከመደባይ ሕዝብ ከድግኑ ነገድ ከአባቱ ተስፋነ መስቀል እና ከእናቱ ታድህነ ማሪያም ተወለደ። ስሙም እስጢፋኖስ ነበር። በ15 አመቱ ድቁና ተቀበለ። እንዲሁም አባ አበክረዙን ተብለው በ16 አመታቸው ከመነኮሱ በኋላ አባ እስጢፋኖስ ወደ ገዳማቸው እንደመጡ ይጠቁመናል። አባ አበክረዙን አባ እስጢፋኖስ ወደገዳማቸው የመጡት ከመነኮሱ በኋላ ቢሆንም በመንፈሳዊ ተጋድሏቸው አርአያ ከሆኗቸው የገዳማቸው መነኮሳት መካከል ቀዳሚው አባ እስጢፋኖስ ናቸው። አባ አበክረዙን ወደ አባ እስጢፋኖስ እየሄዱ ይማሩ ነበር። አባ እስጢፋኖስ ስለሃይማኖታቸው በተለይም መነኩሴ እንዴት መኖር እንዳለበት የተጻፉ መጻህፍትን በመመርመር መጻህፍቱ በሚያዙት መሠረት ይኖራሉ እንጂ የመነኮሳቱን የልማድ አኗኗር አይከተሉም። አባ እስጢፋኖስ መጻህፍቱ ከሚሉት ውጭ ከሌሎች መነኮሳት ጋራ በማንኛውም ጉዳይ ማውራት አይፈልጉም። ከቻሉ አለማድመጥን፤ በግድ ከሰሙም ዝምታን ይመርጣሉ።

አባ እስጢፋኖስ ደግሞ ጥብቅ የሆነ ክርስቲያናዊ ስነምግባርን ይከተላሉ። የብህትውና ኑሮም ጥብቅና መጽሀፍ ቅዱሳዊ መሰረት ያለው መሆን ይገባዋል ባይ ናቸው። የመነኮሳቱ ልማድ በአባ እስጢፋኖስ ዘንድ ቦታ ስለሌለው ቅሬታ የነበራቸው መነኮሳት ነበሩ። ቅሬታቸውን በቅኔ በአሽሙር መልክ"የደብሩ ልማድ ያልሆነ የሚያደርግ"[12] ሲሉ ተቀኙ። የአባ እስጢፋኖስ መልካም ጠባይ እና የጽድቅ ስራ ነው እንጂ እንደተቀኙት ቅኔ አይደለም ሲሉ አባ አበክረዙን ተቃወሙ። ከዚህ ተቃውሞ በኋላ በአባ እስጢፋኖስ ከሳሾች ዘንድ አባ አበክረዙንም ከአባ እስጢፋኖስ ወገን ተደመሩ። አበምኔቱ ዘንድ አባ እስጢፋኖስ "በደብሩ ልማድ ባልሆነ በራሱ ምክር ይሄዳል፤ ደግሞ ሌሎችን ወደ ባህታዊነት ትምህርት ይስባል" ሲሉ ከሰሱት። አባ እስጢፋኖስን የሚከተሉትን ኣባ አበክረዙንና ሌሎቹን ተከታቹን ከመስዋእት እና ከማእድ ያባርሯቸው ጀመር።

አባ እስጢፋኖስ ከቆይታ በኋላ በአበምኔቱ እንዲመለሱ አግባቡዋቸው። አባ እስጢፋኖስም እሺ ብለው ወደገዳማቸው ሲመለሱ አበምኔቱና ከሳሾቻቸው አባ እስጢፋኖስን በእግር ብረት አስረው ባዶ ቤት ቆለፉባቸው። አባ እስጢፋኖስ ሲባረሩ አብረው ከገዳሙ ወጥተው ነበር ሲመለሱም

[12] ደቂቀ እስጢፋኖስ ገድለ አባ አበክረዙን ፣ 232

ከአባ እስጢፋኖስ ጋራ ተመለሱ። የገዳሙ አበ ምኔት አባ አበክረዙንን በእጁ በመገፍተር “በጀመረው መንገድ ረዳትና ጓደኛ የሆንከው አንተ አይደለህምን?” ብሎ ከገዳሙ አባረሯቸው። አባ አበክረዙን እና ሌሎች ጥቂት መነኮሳት ከገዳሙ ወጥተው ተሰደዱ። “ስደቱን ተሸክሞ ከእምነቱ ጋራ ሄደ”[13] የሄዱትም “ባህረ ሳፍ(የሱፍ ዛፍ)[14] ድረስ እንደሆነ ይጠቁሙናል።

አባ አበክረዙን እድሜው 33 አመት ሲሆን ዜራ ናቋ ወደምትባል ደብር ሄዱ። አበምኔቱ ማረፊያ ሰጥቷቸው መጽሞና ለመኖር እንዲፈቅዱከላቸው ጠየቁ። በተከዜ ምድረበዳ አንድ ቦታ ሰጥተዋቸው ከተባረሩባት ደብር ሌሎች አራት መነኮሳት ተጨምረው ማህደር አቋቋሙ። አባ እስጢፋኖስም አበምኔቱ ወደተባረሩበት ገዳም እንዲመለሱ በማባበል መልሰው አስረዋቸው ነበር። አገረ ገዢው በማሰራችን ይከሰናል ብለው ፈቱት። አባ እስጢፋኖስ ሲፈቱም አባ አበክረዙን ተቀበሏቸው። ከአባ አስጢፋኖስ ጋራ ብዙ ገዳማትን ጎበኙተዋል። እንዲሁም ብዙ ተከታዮችን አፍርተዋል። አባ እስጢፋኖስ “ እግዚአብሄር እጄን ያሳረፈበት ሰው ይሰጣችኋል” ያለው አባ አበክረዙንን እንደሆነም ይጠቁሙናል። ከነበሩበት ተሰደው ከሄዱ በኋላ በሶስት ተከፈሉ። አባ አበክረዙን ሁሉንም በየተራ ይጎበኛቸው ነበር። አባ እስጢፋኖስም በአጼ ዘርያእቆብ ውሳኔ ከነበሩበት ተባረው በዚያው “ሰማእትነታቸውን ፈጸሙ”።

“ደቂቀ እስጢፋኖስ ወደ መድረክ ከመውጣታቸው በፊት ገዳማት የራሳቸው የአገልግሎት መጻህፍት እንዲደርሱ የየራሳቸውን ደንብ እንዲዘረጉ (እንዲያወጡ)የኦርቶዶክስ እምነትን በራሳቸው እውቀት ልክና በመረዳታቸው መጠን እንዲተረጉሙ ሙሉ ነጻነት ነበራቸው(Getachew 110)[15]።

በ1421 ዓ.ም ንጉሱ አጼ ይስሐቅ ዘንድ አባ እሰጢፋኖስና ተከታዮቻቸው ተከሰው ለክሳቸው ምላሽ እንዲሰጡ ተደረገ። ተከሳሹ አባ እስጢፋኖስ ጳጳሱ ባሉበት ንጉሱ ፊት ቀርበው ከሳሽ ክሱን እንኩዋን በትክክል ሳያስረዳ እግረመንገድ በተነሳ የምንኩስና ህይወት(አኗኗር) ጥያቄ አባ እስጢፋኖስ በሰጡት ቤተክርስቲያኗ በምትቀበላቸው መጻህፍት ማስረጃ በተከሰሱበት አደባባይ ስለ አዋቂነታቸው እውቅና አግኝተው ትምህርታቸውን እንዲያስፋፉ የበለጠ መንገድ አገኙ። ሆኖም ከሳሾቻቸው አዲስ ንጉስ ሲነግስ ክሳቸውን አጠንክረው ንጉሱ አጼ ዘርያእቆብ ጭምር

[13] ደቂቀ እስጢፋኖስ ገድለ አባ አበክረዙን ፤ 232

[14]“ባህረ ሳፍ” የጣና የጥንት ስም እንደሆነ ተርጓሚው በግርጌ ማስታወሻቸው ይጠቁሙናል።

[15] Getachew Haile. 1983. “The cause of the Estifanosites: A Fundamentalist Sect in the church of Ethiopia.” In Religion: Misce11anea: AAU.

አሳዳጆቻቸው ሆኖ ለመስማት በሚዘገንን መከራ ውስጥ እንዲያልፉ እና ተከታዮቻቸውም ገድል እንዲጽፉ እንደተገደዱ ይገልጻሉ። አባ አበክረዙን እና ተከታዮቻቸው እንዲሁም አጼ ዘርያእቆብ እና ከሳሾቻቸው ሁለት ጽንፎች ሆኑ። ይህን በአባ አበክረዙንና ተከታዮቻቸው የተፈጸመውን ገድል ለማስረዳት ከአባ አበክረዙን ገድል ከዐውደ ንባቡ መካከል ኮዶችን ወስደን ትንታኔውን እንመለከታለን።

## 3.1 ጽኑ ነቢይ ሲነሳ እንደዚሁ ጽኑ ንጉስ ያስነሳል[16]

በአባ አበክረዙንና በሌሎቹ የአባ እስጢፋኖስ ተከታይ በሆኑ መነኮሳት ላይ እንደዋንኛ ክስ በአጼ ዘርያእቆብ ዘመን የተነሳው ስግደት ለማን ይገባል የሚለው ነው። ስግደት በአፄ ዘርያዕቆብ እና በአባ እስጢፋኖስ እንዲሁም በተከታዮቻቸው መካከል ለተነሳው አለመግባባት ዋነኛው ምክንያት ነው። ንጉሱን ያንገበገበው የእስጢፋኖስ ለእሱ አለመስገድ፣ አንቱ ያለማለት ሳይሆን “ለሌላ አንሰግድም” የሚለው ትምህርት መሠረት ከያዘ ለንጉሱ የማይንበረከክ የሰዎች ቁጥር መብዛቱ ነው። ይህንንም በንጉሱ ዘንድ ለንጉሱ አሳቢ መስለው ሹመትና መወደድን ከንጉሱ ለማግኘት “እነዚህን እንደዚህ ዝም ካልካቸው ሁሉም የነሱን ፈለግ ይከተሉና ለመንግስትህ ስልጣን የሚሰግድ አይኖርም።” ስለዚህ ንጉሱ የወሰደው አማራጭ እስጢፋኖስን “እስጢፋ” ተከታዮቹን እስጢፋዊያን ብሎ ማግለል አግልሎም ከቤተ-መንግስቱ እና ከቤተ-ክህነቱ ማባረር ነው። ለዚህም የህዝቡን ቀልብ መሳቢያ “ከእግዚአብሄር ሌላ የሚለውን ማፍረሻ ውግዘትና ቅጣት ማጽደቂያ ጠቡን ግላዊ ከማድረግ ከማሪያም ጋር ማድረግ ጠቡ ተቋማዊ ስለሚሆን ለቤተመንግስቱ ወገን ፋይዳው ከፍተኛ ነው። መነኮሳቱን ያን ያህል መከራ እንዲቀበሉ ያደረጋቸው እና በመከራ ያጸናቸው እውን የማሪያም ግዳይ ብቻ ነው ወይ? ስንል አይደሉም ለማለት የሚያስችል ማስረጃዎች እናገኛለን። ለምሳሌ፡-ለማሪያም ስገዱ ቢሏቸው፤ …ማሪያምን ለልጇ ስንሰግድ እዚያ እናገኛታለን[17]። … ለአምላክ እናት ለማሪያም ስግደት ብንሰግድ አያሳዝነንም[18]። ለማሪያም ስገዱ[19]…ለማሪያምና ለሰላም መስቀል እንሰግዳለን አሉ[20]። የአምላክ እናት ሆይ እነሆ ከማህጸንሽ

---

[16] 254
[17] 146
[18] 148
[19] 149
[20] 178

ጥላ ስር ተደምረናል። በጭንቃችን ጊዜ ልመናችንን አትናቂ[21]። በማለት መነኮሳቱ ስለማሪያም ያላቸውን አቋም የሚያሳዩ መረጃዎችን እናገኛለን።

የከሳሾቹ ጥያቄ በሰበካው የሃይማኖት ነው። ውስጡ ግን ተበለጥኩ ወይም ስልጣኔን ልቀማ እችላለሁ የሚል ፍራቻ ነው። አንዳንዴም ሙሉ በሙሉ ሽፋን የሆነው የሃይማኖት ጥያቄ ይረሳና የግል ክብር ለጥያቄ ይቀርባል። ደቂቀ እስጢፋኖሳዊያኑ(ተከሳሹ ወገን) ከጅማሬ እስከ ፍጻሜው የሃይማኖት ጽንሰ ሀሳብን ከተጻፉ የህግ መጻህፍት ማስረጃ በመጥቀስ የምንኩስና ህይወት በመመሪያው መሰረት መሆን አለበት የሚሉ ናቸው። ሲከሰሱ የሚያቀርቡት ማስረጃ ከሳሽ መነኮሳቱ እንዲሁም ፈራጅ የሆኑት ሀገረ ገዢዎችና ንጉሱ ጭምር የሚከተሉት ሃይማኖት የተቀበሏቸው መጻህፍት ናቸው። መጽሀፍቱን የተረዱበትን አንድምታ በማንኛውም ሁኔታና እንደጠያቂው ወይም እንደከሳሹ ማህበራዊ ዳራ የሚቀየር የሚለዝብ ወይም በፍርሀት የሚሻሻል ወይም ማስመሰል ያለበት ሳይሆን የማይቀየር አቋም የሚያመለክት ነው።

አባ አበክረዙንን እና መሰል አቋም ያላቸውን መነኮሳት እንዲሁም ሌሎችም የሃይማኖቱ ተከታዮች የተለያየ መከራ ይደርስባቸዋል። ለምሳሌ ያገሏቸዋል፣ "እስጢፋኖስ እርኩስ ነው ብለው። አዎን፣ እርኩስ ነው ሲልህ፣ ሰላም በለው በእንግድነትም ሲመጣ በእህልም በውሃም ተቀበለው። አለዚያ ከ(እስጢፋኖስ)ልጆች(አንዱ) እንደሆነ እወቅ[22] የሚል አዋጅ ጭምር ታውጆባቸዋል[23]። ይከሰሳሉ፣ ይንገላታሉ፣ ይዘረፋሉ፣ ይደበደባሉ፣ ይገደላሉ። ሆኖም ሀሳባቸውን የሚደግፉ ግን ፊት ለፊት መጋፈጥ የማይፈልጉ ከለላ የሚሰጧቸው የሃይማኖቱ ተከታዮች በርካታ ናቸው። ፊት ለፊት የሚጋፈጡት መነኮሳት መሪ እና መከራ ሲደርስባቸው ከሚያጽናኑዋቸው ግንባር ቀደሙ አባ አበክረዙን ናቸው።

ትግሉ በስልጣን እና በእምነት መካከል ያለ ሲሆን "ለአመንኩበት እምነት እሞታለሁ" የሚለው እና "እኔ ያልኩት ካልሆነ በምድር ላይ ማድረግ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ" የሚል የንጉስ አቋም የያዙ ተመጣጣኝ ሀይሎች ናቸው። ተከሳሾቹ እነ አባ አበክረዙን (ደቂቀ እስጢፋኖሳዊያን) ለአመኑበት እውነት እስከ ሞት የጸኑ ሲሆን፣ ከሳሽ መነኮሳት እና ንጉሱ ሲሆን በተለይ ንጉሱ እኔ ያልኩት ካልሆነ በስተቀር የትኛውንም በሀይል፣ በገንዘብ፣ በስልጣን ማድረግ የሚችለውን ሁሉ

---

[21] 140

[22] 167

[23]በንጉሱ አዋጅ ደቂቀ እሰጢፋኖስ እንኳን ከቤተክርስቲያን ከቤተ ምእመናንም እንዳይገቡ ክልክል ነው 136።

ከማድረግ ወደ ኋላ የማይል ነው። የህይሉን መመጣጠን ተከሳሽ መነኮሳቱ ተረድተው ይመስላል ስለራሳቸው እና ስለከሳሾቻቸው " ጽኑ ነቢይ ሲነሳ እንደዚሁ ጽኑ ንጉስ ያስነሳል" ብለው የተናገሩት።

## 3.2 ከእግዚአብሔር የተሰጠችውን ጸጋ ከሌላው ዘንድ ሲያይ የሚቀና ነፍሰ ገዳይ ነው[24]

አባ አበክረዙን ምንኩስና የሚያዘውን አኗኗር በመኖር ሌሎችን በማስተማር ሃይማኖታቸውን ማስፋፋት አባ አበክረዙን "የሚፈልጉት የአባታቸውን ፈለግ መከተል። እንደሱም ከመስቀል ላይ መውጣት፣ የሃይማኖታቸው ስብከትም በምድር ሀገሮች ሁሉ እንድትጸና ነበር።[25]" ይህንን አቋማቸውን ያወቀው ንጉሱ እንዲህ ሲል ጠይቋቸዋል። "የአባታችንን አንተውም የምትሉት ትእቢታችሁ ምንድን ነው? ዳግም ሌሎችን ወደ ትምህርታችን እንመልሳለን ትላላችሁ። አሁንም አባታችሁ ውሻ ነው። እናንተም ሰየጠራን የምትጋልቡ ውሾች ናችሁ። ለምን እንደሰው ሁሉ አታደርጉም?" ሲላቸው ምላሻቸው ይህንን የማስፈራራትም የማባበልም ጥያቄ እንደማይቀበሉ የሰጡት ምላሽ ቀደም ሲል ብዙ መከራ መቀበላቸውን የሚያመለክት ነው። ይሄውም ..."በምን ምክንያት ሆነና ነው በህይወታችን ዘመን ሁሉ የምንገረፈው፣ የምንሰደበው፣ የምንሰደደው፣ በዚህ ምክንያት አይደለምን? እኛ ለእግዚብሄር ካልሆነ ለማንም አንሰግድም[26]።

በአባ አበክረዙን ላይም እንደ አባ እስጢፋኖስ ሀገረ ገዢዎች ዘንድ እየከሰሷቸው የምንኩስናው ደንብ በሚያዘው መሰረትለመኖር አልቻሉም። በገዳማቸው ለመኖር እንኳዋን አልተፈቀደላቸውም። አባ አበክረዙን አባ እስጢፋኖስ ከሞቱ በኋላ የአባ እስጢፋኖስን ጥብቅ የምንኩስና ህይወት አስቀጣይ መምህር ሆነው ሌሎችን እያስተማሩ እና ከከሳሾቻቸው በሚደርስባቸው መከራ እያጽናኑ በሃይማኖታቸው እና በአቋማቸው እንዲጸኑ ያበረታቷቸው ነበር። አባ እስጢፋኖስ ይኖሩበት የነበረው ገዳም አበ ምኔት ጀምሮ እስከ ንጉሱ የተከሰሱበት ክስ በአባ አበክረዙንና በሌሎቹ ደቂቀ እስጢፋኖሳዊያን ከበፊቱ በጠነከረ መልኩ ቀጥሏል። ሆኖም የክሱ ጭብጥ ምንም ልዩነት አልነበረውም።

[24] 259
[25] 241
[26] 136

አባ አበክረዙን እና ሌሎቹን ንጉሱ ፊት በሰበብ አስባቡ የሚከሷቸው ሃይማኖቱ ጉዳያቸው ሆኖ ሳይሆን ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ነው። በመነኮሳቱ ሰበብ ንጉሱ ፊት በመቅረብ ሹመት የሚፈልጉ መነኮሳት ናቸው። ለንጉሱም ስለእነ አባ አበክረዙን እንዲህ ብለው ነገሩት “መምህራቸው አበክረዙን ነው፤ ከቀድሞው አባታቸው የጸና እና የከፋ ነው” ንጉሱ ይህንን ሲሰማ በጣም ተቆጣ። ቁጣውንም ለማብረድ አባ አበክረዙንን እና ተከታዮቻቸውን የሚኖሩበት ገዳም አገረ ገዢ እንዲልካቸው መልእክተኛ ላኩ። ከንጉሱ ትእዛዝ የደረሰው አገረ ገዢ “…ሄዶ ቅዱሳኑን ያዛቸው። …አቡነ አበክረዙንንም አጥብቀው ፈልገውት ነበር። ግን እግዚአብሔር ከዓይናቸው ስለሰወረው አላገኙትም።[27]” ንጉሱ ዘንድ የቀረቡት የአባ እስጢፋኖስ ተከታዮች በየሀገሩ ባሉ እስር ቤቶች[28] እንዲታሰሩ ንጉሱ ትእዛዝ አስተላለፈ።

አባ አበክረዙን ከአባ እስጢፋኖስ ጋራ በመሳሳይ ዘመን የነበሩ ቢሆኑም አባ አስጢፋኖስ በአደባባይ ለክስ የቀረቡትን ያህል አልቀረቡም። ንጉሱ የተከታዮቻቸው መብዛት አሳስቦት በተደጋጋሚ ፊቱ እንዲያቀርቡዋቸው መልእክተኛ ብልክም አልተሳካለትም። “አባ አበክረዙንን ያመጣ እኛ ዘንድ ክብርና ሞገስ ያገኛል። የሀገር ሹም ከሆነም ሳይለወጥና ግብር ሳይከፍል ሰባት አመት ይኑር[29]። ንጉሱ አባ አበክረዙንን ያገኘ ይሸለማል ሲል አባ አበክረዙን እድሜያቸው 74 አመት ነበረ። ንጉሱን ይህን ያህል አባ አበክረዙንን ከፈለገባቸው ምክንያቶች መካከል የተከታያቸው መብዛት በተለይም የገዛ ልጁ ጭምር የአባ አበክረዙን ተማሪ እንደሆነ ባወቀ ጊዜ ነበር። የአጼ ዘርያእቆብ ልጅም የደቂቀ እስጢፋኖስ ተከታይ ነው። የንጉሱ ልጅም ከእነሱ ጋራ አለ[30]።

የአባ እስጢፋኖስን ፈለግ በማስቀጠል በእድሜም ከአባ እስጢፋኖስ በላይ የኖሩ እና በየሀገሩ በድብቅ እየዞሩ ተከታዮቻቸውን እንዲበዙ እና በመከራ እንዲጸኑ በማድረግ ይታወቃሉ። “ትክክሉ የመንፈስ አባቱን ነገር መጠበቅ የቃሉን ምስክርነት ልብ ማለት (ባባቱ) ቁመት ልክ ለመቆም እስኪደርስና ከፍ እስኪል ድረስ የፈለጉን መአዛ መከተል ነው[31]። ሲሉም ገልጸዋል።አባ አበክረዙን በመከራ ውስጥ ማለፋቸው፣ የእድሜ ባለጸጋ መሆናቸው ካነበቡት የሃይማኖት

---

[27] 241

[28] እስር ቤቶቹ የተለያዩ ናቸው። በአባ አበክረዙን ገድል ውስጥ  ለምሳሌ በስም የሚጠቀሱት እስርቤቶች ጉንጽ፣ ዳትር፣ ሳጉራይገኙበታል።

[29]254

[30] 254

[31] 258

መጻህፍት ያገኙት እውቀት ከህይወት ልምዳቸው ጋራ ተዳምሮ ተከታዮቻቸውን ለማጽናናት፣ ለማስተማር የሚናገሯቸው ንግግሮች ጠንካራና ፍልስፍናም ጭምር ነው። ለምሳሌ “ከእግዚአብሔር የተሰጠችውን ጸጋ ከሌላው ዘንድ ሲያይ የሚቀና ነፍሰ ገዳይ ነው”[32] የሚለውን የተናገሩት አባ እስጢፋኖስም ሆኑ እሳቸው እንዲሁም ተከታዮቹ በሙሉ ትክክለኛውን መንገድ መርጠናል። ከሳሾቻችን እኛን ይህን ያህል መከራ የሚያደርሱብን “በተሰጠን ጸጋ በመኖራችን የቀኑ ናቸው” የሚል እምነት አላቸው። መቅናትን ደግሞ ከነፍስ ማጥፋት ጋራ በማነጻጸር ገልጸውታል። ሌሎችም በርካታ ሊተነተኑ የሚችሉ ንግግሮችን በገድላቸው ውስጥ እናገኛለን። የገድሉም ጸሀፊ የሚነግሩን መመዝገብ የቻልነውን ብቻ ጻፍን እንጂ ሁሉ አልተመዘገበም በማለት ይነግሩናል። በዘመኑ የነበረውን የአባ አበክረዙንን እና የተከታዮቻቸውን አኗኗር በተመለከተ ከተናገሩት መካከል ጥቂቶቹን እንደሚከተለው እናነባቸዋለ።

### 3 3 ድህነት ስሩ ግጭት ነው[33]

አባ አበክረዙን የሚበሉት የሚጠጡት፣ የሚጸልዩበት ቦታ እስኪያጡ ድረስ የተለያየ መከራ አሳልፈዋል። የንጉሱ መልእክተኞች አባ አበክረዙንን ፍለጋ ብዙ ገበሬ አሰቃይተዋል። ሰብላቸውን አቃጥለዋል፣ መኖሪያ ቤታቸው ወድሟል። መነኮሳቱ የለፉበትን እርሻ ተነጥቀዋል። በዚህ ምድር ላይ አንድ ሰው ሌላው ላይ ማድረግ የሚፈልገውን ሁሉ አድርሶባቸዋል ቢባል የሚጋነን አይደለም። ለምሳሌ አባ አበክረዙን ከሸመገሉ በኋላ በአንድ ዋሻ ሳሉ የንጉሱ መልእክተኞች “...ልብሳቸውን ስንቃቸውን የድህነት ገንዘባቸውን፣ የሸማግሌውን ደበሎ ሳይቀር ገፈፏቸው...በዋሻ ውስጥ ያለን የሳር መኝታ በእሳት አቃጠሉት[34]። አባ አበክረዙን ከዚህ ተነስተው ይመስላል ዛሬም ቢሆን በዓለም ላይ በሰላም እጦት የሚመጣውን ድህነት ጭምር በአንድ አረፍተ ነገር ሲገልጹ “ድህነት ስሩ ግጭት ነው” በማለት ነበር። በእሳቸው እና በመነኮሳቱ ላይ የነበረው ጥላቻ የፈጀውን ጊዜ ያበከኑትን የሰው ሀይል፣ የተቃጠለውን ሀብት አስበው ይመስላል ይህንን ዘመን ተሻጋሪ አባባል የተናገሩት።

የመነኩሴ ግዴታው አይኑን ጨፍኖ በእምነት መታገል ነው[35]። ሲሉም መከራቸውን ሁሉ የተቀበሉት ስለገቡበት የምንክስና ህይወት ብለው እንደሆነ ለሚያሳድዷቸው መነኮሳት ጭምር

[32] 259
[33] 262
[34] 255
[35] 262

የሚጠቅም አባባል ተጠቅመው ህይወቱን ገልጸውታል። መከራው ከሌሎቹ መነኮሳት በበለጠ ለምን እንደጠነከረባቸውም ተከታዮቻቸውን ለማጽናናት የተጠቀሙበት አባባል"....እውቀት ባላቸው በረጅሙ በሚያስቡ የጽድቅ ስርዓት ትጠነክርባቸዋለች[36]።" ነበረ። ከሳሾቻቸው እነሱን ለመክሰስ ነገር ሲያወጡ ሲያወርዱ ጊዜ መውሰዳቸውን በማስታወስ እነሱም ምንኩስናቸው ለጽድቅ ተብሎ ቢሆንም ጽድቅ ግን በዚያ መንገድ እንደማይገኝ ሲገልጹ "የፅድቅ ስርዓት በስራ እንጂ በነገር አይታነጽም[37]። በማለት ከዚህ አባባላቸው ጋራ አያይዘው ሰፋ ያለ ሀተታም አክለው ፍልስፍናቸውን አሳይተውናል።ከናንተ በኋላ ለሚመጡ ምስክር እንዲሆን አይተውም እንዲደሰቱበትና እንደዚያ እንዲያደርጉ፣ ከናንተ በፊት ስለነበሩት ወንድሞቻችሁ ገድልና ጻማ ሁሉ አሁን ጻፉ። ያሉትም አባ አበክረዙን ናቸው።.......ምን ያሳዝናችኋል? ተስፋችን ስለ እግዚአብሄር መሞት ነው። አሁንም ለመነኩሴ በስርዓቱ እንዳለ ከመሞት የሚሻለው የለም።(267 ላይም ይደገማል)....ስርዓት ለሚሞትላት ነች። ሌሎችም በየገጹ የምናገኛቸው በርካታ[38] አባባሎች አሏቸው። በ 81 አመት ታቸው አረፉ። የገድሉ ጸሀፊው ይመስለኛል "እነዚህን የያዝናቸውን ጥቂቶቹን ከማስታወስ በቀር ሁሉንም ለማጽናት አልቻልንም በማለት ገድሉን ጽፎ ያጠናቅቃል።

## 4. ማጠቃለያ

የአባ እስጢፋኖስ ተከታዮች "ለአመኑበት እውነት መሞትን የማይፈሩ ነበሩ።" አባ አበክረዙንም ተቀብለዋቸው ትምህርቱን ከግለሰብ ወደ ተቋም አሸጋግረውታል። ተቋሙም ደቂቀ እስጢፋኖስ ለመባል በቅቷል። በደቂቀ እስጢፋኖስ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ ሶስት ገድሎች የተቋሙ ውጤት ናቸው። አባ አበክረዙን ጽናቱን ከየት አመጡት ስንል ከዚሁ ከገድሉ ከተመለከትናቸው አኗኗሩና ጠባዩ ምላሽ እናገኛለን። እንዲሁም ገዳማት የየራሳቸውን ደንብ እንዲዘረጉ(በተረዱት መጠን ማሰብ) የመመራመር ነጻነት ነበራቸው ማለት ነው። በዚህ መሠረት የያዙት አባ አበክረዙን መጻህፍቱን ከመረዳትም አልፎ ይፈላሰፍባቸው ነበር። የደቂቀ እስጢፋኖስ ታሪክ ቢነቀፍም ቢወደስም የሀገራችን ታሪክ ነው። ቅዱስ ዳዊትንና ንጉሥ ሰሎሞንን ያክል ታላላቅ ነገሥታትም

---

[36] 263

[37] 264፣ 265

[38] ህዝባውያንን ማየት የመነኮሳትን ልብ ያደክማል 267፣ ነገ የምትወልደውን አናውቅም፣ 269። በእጃችሁ ስራ ኑሩ 269 1. በጽድቅ ስርዓት መታገል፣ 2. በነገስት አደባባይ የሰማእትነት መንገድ፣ 3.ደጎች አባቶች በገለጡት በገዳም መዘጋት፣ ለሥርዓቱ ምንም እንከን እንደሌለበት እኔ(አባ አበክረዙን ማለት ነው) ምስክር ነኝ 271... እነዚህና ሌሎችም ሊተነተኑ የሚችሉ አባባሎቸ አሏቸው።

ከጠንካራ ጎናቸው ጎን ለጎን ደካማ ታሪካቸው ሰፍሯል፡፡ የኛ ነገሥታትም ታሪክ በዚያ መልክ በጎና ጸያፍ ተግባራቸው መጻፉ መልካም ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

**ይሁንታ**

የአቀራረብ ስልቱ ቋንቋው (ቃላት፣ ሀረጎች፣ ሰዋሰዋዊ አወቃቀር)ከነባህሉ እና እሴቱ (ዘይቤዎች፣ ድምጸቶች፣ ምሳሌዎች፣ ትእምርቶች)ከነሙያቸው፣ ከነምግባራቸው (ማሳመን፣ ተግሳጽ) ሊጠኑ ይችላሉ፤ ሊጠኑ ይገባል።

**ዋቢ ጽሁፎች**

ከገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ(ዘአጠሞ መምህር ወማህበር ዘጉንዳጉንዶ ደብረ ገሪዛን ማሪያም ገዳም፣ 1996።

ብርሃኑ ገበየሁ (1999)፡፡ የአማርኛ ሥነግጥም፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ኪዳነወልድ ክፍሌ። 1948።መፅሐፈ፡ ሰዋሰው፡ ወግስ፡ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ።

Crawford, VM 1961 The legends of the saints: An introduction to Hagiography: translation from French.

Getachew Haile. 1983. “The cause of the Estifanosites: A Fundamentalist Sect in the church of Ethiopia.” In Religion: Misce11anea: AAU.